# PANORAMA # XXIII

## የትዝብት አድማስ

ግንቦት 1 2000 ዓም

## ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

የሥነ አዕምሮ ጠበብት እንደሚያስረዱት ከሆነ÷አንድ ሰው ሁል ጊዜ ሌላውን የሚጠላ÷ የሚፈራና የሚጠራጠር ÷ በእርሱ በራሱ ላይ እራሱ ያላወቀው የውስጥ ደዌ ስለአለበት ነው ይላሉ:: በአመዛኙ በሽታው የአካል ሳይሆን÷ የአዕምሮ ሳይሆን አይቀርም ይባላል:: ታዲያ ይህ ግለሰብ የዚህ ደዌ ሰለባ ሆኖ የሚቀረው ደግሞ÷ እራሱን ስለሚጠላ÷ ሰለሚፈራና ስለሚጠራጠርም ጭምርም ነው ተብሎም ይገመታል:: ራሱን የጠላ ሰው ደግሞ ሌላውን ይወዳል ተብሎ የሚጠበቅ አይሆንም:: የዚህ የሥነ ልቦና ተጎጅ የሆነ ሰው በራሱ ውስጥ የተደበቀ የዝቅተኝነት ስሜትን ስለሚያስተናግድ÷ ኅብረተሰቡን ሁሉ እንደ ደመኛ ይቆጥረዋል:: ሁሉ የሚጠላው÷ የሚጠራጠረው÷ የሚያገልለው÷ የሚበድለው ይመስለዋል:: ዘለዓለም በፍርሃት÷ በጥርጣሬ÷ በጭንቀት÷ በቁጭትና በንዴት÷ እየተብተከተከ÷ በጥላቻ እየተቃጠለ÷በቅናት እየበገነ÷ በቁጣ የደበነ መላ ይህወቱን ያሳልፋል:: ከፍቅር÷ ከርኅራሄ÷ ከወዳጅነትና ከልማት ይልቅ÷ ጠብን÷ ጥላቻንና ጥፋትን ይፈልጋል:: ያራምዳል:: ቂምንና በቀልን ተሸክሞ የህይወቱ መመሪያ አድርጎ ይጓዛል:: ይቅርታና ምህረት የሚባሉ ነገሮች ሲያልፉም አይነኩት:: ለኅብረተሰብ የሚጠቅም አዳዲስ ኃሳቦችን በማፍለቅ ከመስራት እየተቆጠበ÷ በአለፈው መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ ብቻ እየተሽከረከረ÷ የዳፍንት ኑሮውን ይገፋል:: ሌት -ተቀን ጠላቶቸ ናቸው በሚላቸው ክፍሎች ላይ የጥቃት ፍላጹን አነጣጥሮ ከተቻለው ለመበቀል ካልሆነለት ደግሞ÷ አጥፍቶ ለመጥፋት ዘወትር ተሰናድቶና አድፍጦ ይጠብቃል::

የዚህ ዓይነት ሰብዕና ያለው ግለሰብም ይሁን ቡድን ዓላማውን ለማራመድ የሚያስችለውን ሥልጣንና ምቹ ጊዜ ከአገኘ÷ የተደበቀ ዓላማውን ለመምታት ጊዜ አይፈጅበትም:: በታሪክ እንደተረጋገጠው በአመዛኙ አምባገነኖች የነዚህ ባኅርያት ነፀብራቆች ናቸው:: ስታሊን÷ሂትለር÷ሙሶሊኒና÷ በኛው ሀገር መንግሥቱ ኃይለማርያምና በወያኔ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅት የተሰባሰቡት ግለሰቦች እንደ ምሳሌ የሚቆጠሩ ናቸው:: ለአያሌ ዓመታት አምቀው የያዙትን ምናነትና ማንነት÷ ምኞትና ፍላጎት÷ ኅልምና ቅዠት በተግባር ለማሳካት የሚያስችላቸውን የመንግሥት ሥልጣንና ኃይል ከጨበጡ ÷ በድሎናል ብለው የፈረጁትን ኅብረተሰብ ለመበቀል የሚያግዳቸው የሞራልና የኅሊና ትዝብት አይኖራቸውም:: ለጭካኔያቸው ገደብ÷ለክፋታቸው ወሰን የላቸውም:: ለታሪክና ለትውልድ ፍርድ አይጨነቁም:: ሕዝብን ስለሚፈሩና ስለሚጠሉ አምቀው የያዙትን መጥፎ ባኅርይ በመጠቀም÷ ሀገርን ማጥፋትና ሕዝብን

*መበደል ሥራየ ጉዳየ ብለው ይይዙታል። ጥላቻና ፍራቻ፥ ቂምና በቀል እየተፈራረቁ ባጎሪያቸውን ይመርዙባቸዋል መንፈሳቸውንም ይረብሹባቸዋል። ሕዝብ እየገደሉ ተቃዋሚያቸውን በመጨፍጨፍ የንፁሃንን ደም በአፈሰሱ ቁጥር በእጃቸው ላይ የሚገኘው የጓጎለ የንፁሃን ደም ያሳብዳቸዋል። ሰላምና ዕረፍት ይነሳቸዋል። የገዛ ጥላቸውን እየፈሩ፥ በስጋት እየደነበሩ፥ የመከራ፥ የጭንቀትና የፍርሃት ኑሮ ይገፋሉ።*

*ስለ ሂትለርና ሙሶሊኒ፥ እንዲሁም ስለሌሎቹ አምባገነኖች ታሪክ አያሌ ስንክሳሮች የተፃፉ ስለሆነ ወደዚያ ማተኮሩን አንመርጥም። " የራሷ ሲያርርባት የሰውን ታማስላለች" የሚለውን ይትብሃል በግምት ውስጥ በማስገባት ብቻ ሳይሆን፥ ስለራሳችን ሀገር ሁኔታ ተናግረን ተናግረን ያልጨረስነው ስለሆነ፥ ስለእኛው መከራና ስቃይ መናገራችንን እንቀጥላል። ይህንንም የምናደርገው፥ በደርግና በወያኔ ድርጅቶች ውስጥ ስለነበሩት/ስለ አሉት ግለሰቦች ባኅርይና ድርጊት አዲስ ግኝት ተገኝቶ ስለርሱ ለመተንተን ሳይሆን፥ ኢትዮጵያና ዜጎቿ በነኝህ ሁለት ተፈራረቂ ቡድኖች ምክንያት ምን ያህል ተመሳሳይ ጥፋትና በደል፥ መከራና ስቃይ ፥ ጥቃትና ውርደት፥ እንደተፈፀመባቸው ለማስመዝገብ ነው።ይህንን ለማድረግ የምንጥረውም፥ ልክ እኛም እንደነርሱ፥ ለበቀል መፈፀሚያ የሚሆን ማጠየቂያና ድልዳል ለማዘጋጀት ሳይሆን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትና የሚደርስበት ንቀትና ውርድት ምን ያኅል ስር የሰደደ መሆኑን ተገንዝበን የወያኔ አገዛዝ ሀገራችንን አጥፍቶ ከመጥፋቱ በፊት ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ተባብሮ በመነሳት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፥ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሚያስችለውን አስቸኳይ መፍተሄ አበክሮ እንዲያስብበት ለማሳሰብ ነው።*

*በመሠረቱ፥በደርግና በወያኔ ተቋማት የተሰባሰቡት ግለሰቦች በድርጊትና በባኅርይ የሚመሳሰሉበት በርካታ መስፈርቶች ቢኖሩም፥ እናም ደግሞ በመጨረሻው ኢትዮጵያን አጥፍቶ-የመጥፋት የታሪካቸው ምዕራፍ መደምደሚያ መሆኑ የተወቀ ቢሆንም፥የሚለዩአቸው ነገር ቢኖር፥ በመነሻ ደረጃ፥ ደርግ ኢትዮጵያን አጥፍቸ እጠፋለሁ የሚል እንዳልነበር ነው። ወያኔዎች ግን ሀ ብለው የተነሱትና በዕቅድም ተዘጋጅተው የመጡት ሀገሪቱን ለመከፋፈልና ዜጎቿንም ለመፈታተን እንደሆነ በተግባር ያስመሰከሩት ሀቅ ነው ።*
*ሁለቱም አምባገነኖች በመሆናቸው ሕዝብን ፈርቶ በመጥላት፥ ንቆ በመጉዳት፥ ሀገርን በመክዳት፥ ለባዕዳን በመገዛት ተመሳሳይ ናቸው ለማለት የሚቻል ቢሆንም፥ ይሁነኝ ብሎ ሀገርን ከማጥፋት አንፃር፥ ሁለቱም የማይናቅ ልዩነት አላቸው ለማለት ይቻላል። ደርግ እራሱን በክፉ መካሪዎች አስከብቦ የጥፋት እርምጃዎች በመውሰዱ ከመጥፎ አማካሪዎቹ ጋር ተያይዘው ጠፉ። ሀገሪቱንም አጥፍተው እነርሱም ወደ ማይቀርላቸው የታሪክ ጉድጓድ ገብተው ከሰሙ። አረመኔው ደርግ ለጭካኔ ባዳ ባይሆንም የክፉ መካሪዎች ሰለባ ስለነበር ፥ አውቆትም ሆነ ሳያውቀው፥ ወዴት አቅጣጫ ሲሄድ እንደነበር ተረድቶትም ይሁን ሳይረዳው፥ ሀገሪቱ አሁን ለምትገኝበት የጥፋት ጠርዝ አድርሶ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን ድምጥማጥ ለማጥፋት ተዘጋጅቶ ለመጣው ለወያኔ*

አስረክቦ ኮበለለ። መንግስቱ ኃይለ ማርያም በድንቁርና ላይ የተመሠረተ ንቀትና ማህይማዊ ድፍረት ተደራርበውበት ስለነበረ፥ ለትንሽ ጊዜ እንኳን ቆም ብሎ በማሰብ የኢትዮጵያ መሠረታዊና ዘላቂ ወዳጆች እነማን ናቸው? በዘለቄታ መልኩስ የሀገሪቱ ጠላቶች የትኞቹ ናቸው ? ብሎ ለመጠየቅ አልቻለም። ይህ ዕውቀትና ብልኅነት፥ አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት ደርግ የተባለው ጉድ ጨርሶ ሰለአልነበረው፥ለኢትዮጵያ የሚሰውሏትን እየጨፈጨፈ፥ ጀርባዋን በጩቤ የሚወጓትን ግን ሲያሽሞነሙን ቆየ ።እነርሱም ጊዜ ጠብቀው ጉድ ሰሩት። እርሱም ወደ ሚጠብቀው የውርደትና የሀፍረት ጉድጓድ ገብቶ ቀረ።

የደርግ ሰለባ የነበሩት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ግን፥ ጭፍጨፋውንና ጥቃቱን ተቋቁመው፥ አሁንም ኢትዮጵያን ከወያኔ ጥፋት ለማዳን በሚደረገው ትግል ዓይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። በትግል ፀንተው የሚታገሉት ቁርጠኞቹ ሀገር ወዳድ ዜጎችም፥ ድርጅቶችን ከአባላት፥ ጠባብ ብሔረተኞችን ከትግራይ ሕዝብ፥አባገነኖችንም ከሀገር ለይተው በመፈረጅ፥ማን የሀገር ወዳጅ ማን ደግሞ የሕዝብ ጠላት መሆኑን ጠንቅቀው ይረዳሉ።

ደርግ፥ በሰርቶ አደር ስም ብሔራዊ ወንጀል ሲፈጽም እንደ ነበረ ሁሉ፥ ወያኔ ደግሞ በትግራይ ስም መላ ሀገሪቱን ድምጥማጧን እያጠፋት ይገኛል። ሁለቱም በባዕድ መንግሥታት የተደገፉ በመሆናቸውና በከንቱ የልብ ልብ ስለተሰማቸው ሕዝቡን እየናቁ፥ ዳር ድንበሩን እያስደፈሩ ያስንቃሉ። “ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ” እንዲሉ። ናቂ ወዳቂ መሆኑን ግን ጭራሽ አልተረዱትም። በዕርግጥ ብልኀ ሰውም ይሁን ድርጅት ከደርግ ስህተትና አወዳደቅ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ትምህርት መማር በተገባው ነበር። መሀይሞችና አጥፊዎች ግን ለሀገር -ለወገን የሚጠቅም ትምህርት እንዲቀስሙ ከቶ አይጠበቁም።ያማ ባይሆን ኖሮ፥ የሀገራችን ሁኔታ አሁን ባለበት ደረጃ ባልደረሰም ነበር። በራሱ የማይተማመን ማነኛው ድርጅት ይሁን ግለሰብ፥ ሌላውን ስለሚፈራና ስለሚጠራጠር፥ ሁሉ ጊዜ በመንፈስ ቀውስና በሽብር ናዳ እየባነነ እንዲኖር ይገደዳል። ለዚህም ነው ዛሬ የወያኔ መሪዎች ሆን ብለው የማያቋርጥ ቀውስና ችግር፥ ሽብርና ሁከት በመፍጠር ሕዝቡን የቁም ስቅሉን የሚያሳዩት። ሰው-ሰራሽ የእቃ እጥረት፥ የዋጋ ግሽበትና የገበያ ሁከት እያፈራረቁ የኑሮ ውድነትን ሰማይ-ጠቀስ ያደርሱታል። ይህ ደግሞ ሆን ተብሎ በእቅድ የሚካሄድ የአምባገነኖች የአገዛዝ ስልት ነው። ሕዝቡ ስለ መሠረታዊ ችግሩ እየተወያየ የዘለቄታ መፍተሄ ለማግኘት ወደ ሚያስችለው አቅጣጫ እንዳያተኩር፥ ብሎም ሥርዓቱን ለመቃወም እንዳይዘጋጅ፥ በዕለት ጉርሱና በዓመት ልብሱ ብቻ ተወጥሮ እንዲቀር ያስገድዱታል። ይህ ግን ለብዙ ጊዜ የሚቀጥል አይሆንም። “ የድፍድፍ ድንፋታው ውሃ እስኪገባበት” ድረስ እንደመሆኑ፥ የወያኔ ዕብጠትም ሕዝባዊ አመፅ እስኪመጣ ድረስ መሆኑ የታሪክ ሀቅ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጣና አመፅ ሊገታው ቀርቶ አቅጣጫውን ሊያስለውጠው የሚችል አንዳችም ኃይል አለመኖሩ፥ የየካቲት ስድሳ
ስድስቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አመፅ ህያው ምስክር ነው። የዚያ ታሪካዊ

ክስተት ዳግም-ምፅዓቱ ሩቅ እንደማይሆን፥ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክአ-ምድር አድማስ የሚያንዣብበው የአመፅ ዳመና ያመለክታል። ይህን ለመረዳትደግሞ የተራቀቀ ጠቢባን መሆንን አይጠይቅም።

በወያኔ የብሄረሰብ ድርጅት ስር የተሰባሰቡት ቡድኖች ሲፈጠሩ አንስተው ይዘውትያደጉትንና አሁንም የህይወታቸው ዓይነተኛ ዓላማና ግብ ያደረጉት፥ የመጀመሪያ አጀንዳቸውን በሚገባ በተግባር መተርጎም ነው። ይህ ቀዳማይ አጀንዳቸውም የጠባብ ብሄረተኝነትን ጥቅም ማስጠበቅና ማስከብር መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። በመሆኑም፥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ለእነርሱ ጉዳያቸው አይደለም። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኅላዊ ለመጀመሪያው አጀንዳቸው ማስፈፀሚያና መጠቀሚያ ማድረጋቸው ታዲያ አያስደንቅም።

" ጅብን ሲወጉ አህያን ይጠጉ" እንደተባለው፥ ድኅነትንና ችግርን ለማጥፋት በግድ የመላዋን የኢትዮጵያን የቆዳ ስፋት፥ ሀብትና ንብረት፥ ያለ ይሉኝታ መጠቀማቸው፥ለእነርሱ እንደ ጮሌነትና ብልኅነት እንጅ እንደ ከሀዲነትና ስርቆት አይቆጠርም። የተነሱበትን ዓላማ በትክክል በተግባር መተርጎማቸውን ይኮሩበታል እንጅ አያፍሩበትም። በመሠረቱ፥ ሀፍረትንና ይሉኝታን የማያውቅ ሰው ሀፍረት እንዲሰማው አይጠበቅበትም። በዚህም ምክንያት በኅጠኝነት ወህኒ ውስጥ ስለሚኖሩ፥ ከአድማስ ባሻገር ተመልክተው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ሕይወት ሊያስቡ ከቶ አይችሉም። አይጠበቅባቸውም። ይህ ደግሞ ሊያስገርም በጭራሽ አይችልም።

የወያኔ ባለሥልጣኖች በምኒልክ ግቢ ከገቡበት ቀን አንስቶ የፈፀሙትን፥ የሚታወቀውንም ሆነ የማይታወቀውን ሁሉ ለመዘርዘር ወቅቱ ስለማይፈቅድ ብቻ ሳይሆን፥ የተሟላም ስለማይሆን፥ ወደፊት ጊዜ ሊያሳውቀውና ሊያሳየውም ይችላል። የእኛ ተግባር የሚሆነው ግን በትግላችን ሂደት ማነኛውንም ሀቅና ክስተት እየመዘገቡና እየመረመሩ፥ ለታሪክና ለትውልድ ማስቀመጥና ለምንታገልለትም ሕዝብ ማሳወቅ ይሆናል።ይህ ማለት ግን የምንታገለው ለታሪክ ማስታወሻ የሚጠቅም ሪኮርድ ወይም መረጃ በማስያዝ ላይ ብቻ ይወሰናል ማለት አይደለም። ያለመታከትና ያለማቋረጥ እንደ አስፈላጊነቱም ሆነ እንደ አመችነቱ ይህንን ዘረኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስትራተጂያዊ ጠላት ፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ማንበርከክና የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስገኘት የህይወታችንና የትግላችን አልፋ-ኦሜጋ ነው። ይህንንም ወያኔዎቹ በሚገባ ያውቁታል። የገባንበትን ቃልኪዳን ሳናጥፍ፥ በፅና ትና በቆራጥነት መታገል፥ ወያኔ ብቻ ሳይሆን፥መንግሥቱ ኃይለማርያምም ቢሆን እያነገፈገፈው የተናገረው ሀቅ ነው። በአንድ መሠረታዊ ሀቅ ላይ ግን ታሪክና ምልዐተ-ሕዝብ በዕርግጠኝነት ይስማማሉ። ይኸውም፥ሕዝብን የሚንቅ ሥርዓትና አገዛዝ፥ በመጨረሻ እንጦሮጦስ የሚገባ መሆኑን ነው፡ ወያኔዎቹ፥ ሕዝቡን ባይንቁ፥ የኢትዮጵያን አጥር ባልነቀነቁ! የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቿ ግን ኢትዮጵያን እያከበሩ፥ ዜጎቿንም ሳይንቁ፥ ዳር ድንበሯን ያስከብራሉ። ይህ ደግሞ በነባቢት ሳይሆን ፥ በድርጊት የሚረጋገጥ ይሆናል።

**ጊዜናታሪክም ይፈርዳሉ! የሀገርን ክብርና መሬት የሚደፍሩና የሚያስደፍሩ በሕዝብ ትግል ይቸነፋሉ፤ይወገዳሉ::**